24/11/2008

**ሰዎች ሰው እንፈልግ**

**በአሞራው**

ሰው ማልት ምንድን ነው አልገባኝም ፍቺ
ሰው ስዉን ያሰኘው
መልኩ ነዉ ቁመናዉ
ስራው ነው ጠባዩ ቋሚ መስተንክሩ
አልፈታህ አለኝ የሰው ልጅ ሚስጥሩ
*መለያ ባህሪው ውስጣኔ ምግባሩ*

የሰው ልጅ ሰውነት መለኪያ ሚዛኑ
የእሱነቱን ይዘት የሚተነትኑ
ከቶ የትኛው ነው
ሞልቶ የተረፈው ባለ ጸግነቱ
ኮስማና ያረገው ወይስ ድህነቱ
አሊያም ደግነቱ
ፈገግታና ለዛው ማራኪ ውበቱ
ተናገሮ አናጋሪው
ወይስ ቀና አንደበቱ
የቱ ነው ሚዛኑ የሰው ሰውነቱ
ተመዞ ሚወጣው ህያው አብነቱ
አልገባኝምና የታያችሁ ፍቱ
ሰው ማለት የቱ ነው
ወገኑን ሰባንዳ
አባቱን ሰፍዳ
እናቱን ሰከዳ
ትውልድን
ታሪኩን
አገሩን
ሳልባሌ ዝና ስጠላት የሸጠው
በምስኪኖቹ ላብ ከርሱን ያሳበጠው
በወረቅ ፍልስፍና አገርን ለማፍረስ
ዜጎቿን ለማረከስ
ሃብቷን ለመበዝበዝ ቆርጦ የተነሳው
ሰይጣናዊ ተግባር አርማና መለዮው
ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ የጭካኔ ግብሩ አለምን የናኘው
እሱ ነው ሰው ማለት
ሁሉ እሚሰግድለት
እንደ ጥምቀት ታቦት
ሁሉ እሚያረግድለት
የቱ ነው ሰው ማለት
የግፍ አጋፋሪ
የእልቂትአንደራሴ የሴራ ቀማሪ

የክፋት ሊቃውንት ሰቆቃን አብሳሪ

በዚህ ዱክትርናው
ሃብት ያግበሰበሰ
የንጹሃን ገላ በጥይት ያረሰ
ስንዋይ ስዝና ደምን ያፈሰሰ
የአድሜ እኩሌታን ስጥፋት ያዋስ
ሊመከር
ሊዘከር
ፍጹም ያልታደለ
እሱ ሰው ነው እንዴ ሰውን የገደለ
ይልቅስ ንገሩኝ ሰው ማለት የቱ ነው
ሰው ማለት ምንድን ነው
ገና በልጅነት ሰው መግደል ተምሮ
ትንሹን ትልቁን ባሳር አሳርሮ
ዛሬም እንደትላንት እንደልጅነቱ ጨካኝ ሰው ገዳዩ
ከትንሽ እስከ ከትልቅ
ከሊቅ እስከደቂቅ
ማንንም ሳይለዩ
በጭካኔ ማእበል
በሰቆቃ ገድል
ሁሉን ያሰቃዩ
ያገር አሚካሳ
የትውልድ ሰንካሳ
ብካይ የቆሸሹ የታሪክ አተላ
አገረ ገዢዎች ትንሽ ሆነው ሳል ትልቅ ነኝ የሚሉ
 ባጥፊ ባህሪያቸው ያነንም ይህንም እየጎነተሉ
ነጻ አውጭ ነኝ ያለው
ባውሬነት ባህሪው አቻን ያሳገኘው
በመንታፊ ጣቱ ሃብትን የቆለለው
የወገኔ ተባይ
ያረመኔ ክፉይ
የኢትዮጵያ ስቃይ
መዥገር ደም መጣጩ
አልቂት ዎ መከራ ለእመ ሀገር ያጬ
መኖር ዘይቤ ያሉት ህዝብን እያጋጩ
ያንንም ይህንም እያነጫነጩ
ከርሱን ያደለበ በግፉአን ቁስል
ይህም ሰው ይባላል
የክፉ ቀን ብካይ የገማ እንቁላል
ይሀም ሰው ሆነና እንዳዳምተቆጥሮ አክበሩት ተባልነ
ባፋሽ አጎንባሹ
በተተፋ ላሹ

አያሌ ተባልነ
አየ ስምንተኛው ሽ አያባቅለው የለ
ባንዳም እንደጀግና ይከበር ተባለ
እንደሰራ አይገድል ይህ የእስራኤል አምላክ አያሳየንየለ።

በክህደት ማተቡ በውርደት ሰንሰለት
በይሉኝታአልባነት
በባንዳ እሳቤ

በጨካኝ ስሌቱ በሆዳሞች ዘይቤ
ስልጣኑን የያዘው ያነ አድሮ ቃሪያ
ክፋት ስንክሳሩ የደውየነት ባሪያ
እሱም ሰው ነኝ ብሎ
የጠላውን ገድሎ
በጥብጠ እየጋተን  ያሳርን አተላ የመከራን ኮሶ
ሰው ነው በሉ ተባልን እሱ ከማን አንሶ
አይ ስምንተኛው ሽ የመከራ ኮሶ
አያሳየን የለ በዚያ ባራት ኪሎ መልሶ መላልሶ
እሱ ባለወገን እኛ ወገን አልባ
አነሱ ምርጥ ዘር እኛ ጨርቅ ገለባ
እነሱ ምርጥ ዘር
የኛ ዘር ጎመን ዘር
ሲገፉን ተገፍተን እስከግድግዳው ጥግ
ከምህዋር ሲያስወጡን ተጎተን እንደበግ
ስንቀር መለመላ ተለይተን ከዘመድ
እስቲ እንጠባበቅ መከር  እስኪጠባ
ምጻት እስኪገባ
መቁርጥ ያቃተን ለት ሆዳችን ሲባባ።

ይልቅ ሰው እንፈልግ በቅርብ በሩቁ
ልቀው የሚገኙ ከአልማዝ ከእንቁ
ከወርቅከብረቱ ካጉል ብርቅርቁ
ከብርም ከዩሮም እንዲሁም ከዶላር ከሁሉም ደማቁ

መተኪያ አልባዋን በህይወት መኖርን አጥብቀው የናቁ
እንከን አልባ ጀግኖች
የቀውጢ ቀን ኮከብ
የጀግንነት እርካብ
የሞራል አለቶች
የነጻነት ብርሃን ያርነት ደብተሮች
መንነው የቀሩ እውነተኛ ጀግኖች
የቃል ኪዳን አምባ የእምነት ደብሮች
የአርበኝነት አናት
የነጻነት ፈለግ አርማና ተምሳሌት
የት እንደወደቁ
እንዴት እንዳለቁ
ሞትን የመረጡት፤ ባልባሌ ጊዜ፤ በትናንሽ፤ ሰዎች ከመጨማለቁ
እነሱን እንዘክር
አነሱን እንፈልግ ከወደቁት ስፈር

በደም ባጥንታቸው የቆሚትን አገር
ባንዳ አርንታል ኦና ለከስካሳ መንደር
የጋለሞታ ቤት በሁሉ ሚደፈር
ሰዎች ሰው እንፈልግ ከሙታኖች ሰፈር
ከናቅፋ እስካፋቤት
ተሰነይ አቆርዳት
ካሲምባ እስከ ጠለምት
በሁሉም ማእዘናት

ጀግኖች ባረፉበት
ጎበዝ ሰው እንፈልግ
ከባንዳ ከሃዲው ክብርን የሚታደግ
ያስፈልገናል ክንድ
ጎበዝ ሰው እንፈልግ
ከጥቃት
ከውርደት
ክብርን የሚታደግ

እባካችሁ ሰዎች ጀግናን እናፈላልግ
የሹምባሽን ጎጆ ዶግ አመድ የሚያደርግ
ያስፈልጋል ጀግና
በእምነቱ የጸና
እምየን ከጥቃት ያድናታልና፡፡